# WILL of GOD 316

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ?

*“መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።”* ሮሜ 12:2

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እና መፈጸም በጣም አስፈላጊ ነው። እንደ ኢየሱስ ሁን። *“ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ነውና፤”* ዮሐንስ 6:38። አብዛኛው የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሁሉም አማኞች በተመሳሳይ መንገድ ይሠራል። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ለአማኞች የግል ፈቃድ አለው፣ ይህም በዕለት ተዕለት በታማኝነት ከእርሱ ጋር በሚያደርጉት ጉዞ እያደጉ ሲሄዱ ቀስ በቀስ ይገለጣል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ትችላለህ። ግንዛቤን ይሰጥሀል። *“በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።”* ምሳሌ 3:5-6። ለሁሉም አማኞች የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታውቃለህ። የእሱ ግላዊ ፈቃድ ከቃሉ እና ታማኝ የሆነ የታዛዥነት ሕይወት ጋር የማይጋጭ ጥምረት እንደሆነ ታውቃለህ። ከዚያ የመታዘዝ መሠረት ላይ በመመስረት፣ ለአንተ ያለውን ፈቃድ መወሰን እና መታዘዝ ትችላለህ። አብን ጠይቅ። ከቃሉ፣ ከጥበቡ፣ ከሕዝቡ እና ከሰላሙ መመሪያ አግኝ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስታውቅ፣ ታዘዘው።

**የእግዚአብሔር አጠቃላይ ፈቃድ።** አብዛኛው የእግዚአብሔር አጠቃላይ ፈቃድ በመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዛት፣ መርሆዎች እና ምሳሌዎች ውስጥ ይገኛል። በሕይወትህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ዋናው ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። *”ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው።”* መዝሙር 119:105።

1. ትዕዛዛት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሁሉም አማኞች ብዙ ትእዛዛት አሉ፣ ለምሳሌ፣ *“ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና።”* 1 ተሰሎንቄ 5:16-18። እና *“የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው፤”* 1 ተሰሎንቄ 4:3። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ *“ብትወድዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ።”* ዮሐንስ 14:15። የትዕዛዛቱን አውድ ተረዳ። እግዚአብሔር ኖኅን መርከብ እንዲሠራ ነገረው፣ ዘፍጥረት 6:14። እግዚአብሔር ያንን እንድታደርግ አልነገረህም። እግዚአብሔር ዳዊትን ወደ ኬብሮን እንዲሄድ ነገረው፣ 2 ሳሙኤል 2:1። እግዚአብሔር ያንን እንድታደርግ አልነገረህም። ትዕዛዝን ከአውዱ አታውጣ።

2. መርሆዎች። አንተ መከተል ያለብህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች አሉ። የመልካም መጋቢነት መርህ በሉቃስ 16:1-13 ላይ ይገኛል። የደቀመዝሙርነት ዋጋ በሉቃስ 14 መጨረሻ ላይ ይገኛል። የጠፉ ሰዎችን የመፈለግ መርህ በሉቃስ 15 በሚገኙት ሦስት ምሳሌዎች ውስጥ ይገኛል። እነዚህን እና ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ መርሆዎችን ተከተል።

3. ምሳሌዎች። የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዛት እና መርሆዎች ለህይወትህ የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ይሰጡሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እኛ እንድንከተላቸው ምሳሌዎችን ይዟል። በጣም ጥሩው ምሳሌ የኢየሱስ ሕይወት ነው። የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- *“እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ።”* ዮሐንስ 13:15። የእሱን የትሕትና ምሳሌ መከተል ይገባናል፣ ፊልጵስዩስ 2:3-5። በእሱ ፈለግ መራመድ አለብን፣ *“የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው።”* 1 ጴጥሮስ 2:21። *“በርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ ማንም በርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።”* 1 ኛ ዮሐንስ 2:5-6።

**ማስጠንቀቂያ።** እግዚአብሔር አይዋሽም፣ መዝሙረ ዳዊት 119:160። እግዚአብሔር ቃሉን እንድትጥስ አይመራህም ወይም አይነግርህም። ኢየሱስ እኛን ለማስታጠቅ መሪዎችን ይሰጣል፣ ኤፌሶን 4:11-14። ይሁን እንጂ ብዙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አሉ፣ 2 ኛ ጢሞቴዎስ 4:3-4። እግዚአብሔር ቃሉን እንድትጥስ እየነገረህ እንደሆነ በፍጹም አትመን። እግዚአብሔር ያንን አያደርግም። የቤተ ክርስቲያን መሪ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትታዘዝ ቢነግርህ፣ ያ የሐሰት ትምህርት ነው።

**የእግዚአብሔር ግላዊ ፈቃድ።** እግዚአብሔር ለአማኞች የግል ፈቃድ አለው፣ መዝሙረ ዳዊት 32:8፣ ምሳሌ 3:5-6። የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ፈቃድ ታዘዝ። ከዚያም የእሱን ግላዊ ፈቃድ ለማወቅ፣ እግዚአብሔር እንዲነግርህ በትጋት ጠይቅ። መልሱን ከቃሉ፣ ከጥበቡ፣ ከሕዝቡ እና ከሰላሙ ፈልግ።

**ጠይቅ።** የዳዊትን ጸሎት ጸልይ፣ *"ፈቃድህን እንድፈጽም አስተምረኝ፤"* መዝሙር 143:10። ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ ያሉ አማኞች *"የፈቃዱን ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላችሁ ዘንድ"* ቈላስይስ 1:9 ይሆኑ ዘንድ ጸለየ። ለራስህ እና ለሌሎች የምታቀርበው ከልብ የመነጨ ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እና መፈጸም መሆን አለበት።

**መመሪያ አግኝ።** እግዚአብሔር ግላዊ ፈቃዱን በቃሉ፣ በጥበቡ፣ በሕዝቡ እና በሰላሙ ይገልጣል። ፈቃዱን እንዲገልጽልህ እግዚአብሔርን ጠይቅ። ጸሎቶችህን በሚከተሉት መንገዶች ይመልሳል:-

1. የእግዚአብሔር ቃል። የእግዚአብሔርን ግላዊ ፈቃድ ማወቅ የመደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውጤት ነው። ከቃሉ ጥበብን እና ግንዛቤን ስታገኝ እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ፈቃድ ግልጽ ይሆንልሃል። ከቃሉ ጋር የሚጻረር ነገር እንድታደርግ በፍጹም አይመራህም።

2. የእግዚአብሔር ጥበብ። የእግዚአብሔር ጥበብ የሚመጣው ከመንፈሳዊ መታዘዝ ነው፣ 1 ቆሮንቶስ 2:14-15። *"መልካም፥ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።"* ሮሜ 12:2። ጥበቡን ከእግዚአብሔር ለምን፣ *"ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለርሱም ይሰጠዋል።"* ያዕቆብ 1:5።

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት የሚያስችል መገልገያ ነው። ቃሉን በትክክል በመናገር ወይም በመጻፍ የሚያስተምሩ ሰዎች ሊረዱ ይችላሉ፣ ቈላስይስ 1:28። ከበሰሉ አማኞች ምክር ማግኘት ጥሩ ነው። ከአንድ በላይ አማካሪ መኖር ጥሩ ሀሳብ ነው፣ *"ምክር ሲጓደል ዕቅድ ይፋለሳል፤ በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል።"* ምሳሌ 15:22። የበሰሉ አማኞች ከስህተት ነጻ አይደሉም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመለየት የሚረዳህን ትርጉም ያለው ግንዛቤ ሊሰጡህ ይችላሉ።

4. የእግዚአብሔር ሰላም። የእግዚአብሔር ሰላም ለግላዊ ፈቃዱ የመጨረሻ ማረጋገጫ ነው፣ *"የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ"* ቈላስይስ 3:15። *"ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፥ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።"* ፊልጵስዩስ 4:7። ይህ ሰላም ጸሎትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን፣ መንፈሳዊ ጥበብን እና ከመንፈሳዊ ብስለት ካላቸው አማካሪዎች የተገኘ ግንዛቤን ተከትሎ የሚደረግ ውሳኔ ላይ እግዚአብሔር የሰጠው ጥልቅ የሆነ የትክክለኛነት ስሜት ነው። ሰላሙን ፈልግ እና ጠብቅ።

**ፈጽም።** አንድ ነገር የእሱ ፈቃድ እንደሆነ ስትጠይቅ፣ መልሱ "አይ" ሊሆን ይችላል፣ ልክ ለጳውሎስ እንደሆነው፣ 2 ቆሮንቶስ 12:7-10። "ጠብቅ" ሊሆን ይችላል። "ጠብቅ" የሚለው መልሱ ታላቅ በረከት ሊያስገኝ ይችላል፣ ኢሳይያስ 40:31። የእግዚአብሔር መልስ "አዎ" ሲሆን፣ አስቸጋሪ፣ ተወዳጅ ያልሆነ ወይም ውድ ቢሆንም እንኳን ፈቃዱን አድርግ። ፈቃዱን ከልባችን በማድረግ መደሰት አለብን፣ መዝሙር 40:8፣ ኤፌሶን 6:5-6። በክርስትና ስም ከሚሰበከው የሐሰት መልስ ተጠንቀቅ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደምታውቅ እርግጠኛ ስትሆን ታዘዝ።

---

*የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ?*© 2026 by John D. Morris III በ Acts One Eight የታተመ ነው። ይህንን ሙሉ መግለጫ በማካተት ይዘቱን ሳይለውጡ በነፃ ማተም፣ መቅዳት፣ መለጠፍ፣ በኢሜይል መላክ ወይም በመልእክት መላክ ይችላሉ። የአገልግሎትዎን ወይም የቤተ ክርስቲያንዎን ስም ወይም አርማ በገጽ አንድ አናት ላይ ማከል ይችላሉ፣ እንዲሁም የእውቂያ መረጃዎን በገጽ ሁለት ግርጌ አካባቢ ካለው ጠንካራ መስመር በላይ ማከል ይችላሉ። WillofGod316.org በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ላይ የተመሰረተ ነው። አማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ ለመርዳት የተፈጠረ ነው። ወደ Acts One Eight ኢሜይል መላክ ይችላሉ (ከተቻለ በእንግሊዝኛ) በ:- Hello@Mail316.org። የትርጉም አገልግሎቶች የቀረቡት በ www.ChristianLingua.com። *የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ?* በአርባ ስምንት ቋንቋዎች በነጻ በ www.WillofGod316.org ላይ ይገኛል። በእንግሊዝኛ የተዘጋጁት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከThe Lockman Foundation's New American Standard Bible 1995 ነው። በዚህ ትርጉም ውስጥ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከእንግሊዝኛው